# የ"አኬልዳማ" ንባብ

ይህን አጭር ጽሁፍ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ፣ በቅርቡ "አኬልዳማ" ተብሎ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የቀረበው ድራማ ነው። ድራማው በሶስት ጭብጦች ላይ ያጠነጥናል- የትጥቅ ትግል መምራት ( ባለስልጣናትን እስከ መግደል የሚደርስ)፣ የከተማ ውስጥ ሽብር መፍጠርና ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻ ማካሄድ ። የእኔ ሚና የከተማ ውስጥ አመጽ ማካሄድ ወይም በዘመኑ ቋንቋ "ማሸበር" ነው። ይህን ገፅባህሪ ተላብሼ የሰራሁት ድራማ የተዋጣለት አለመሆኑን ልቤም፣ ድራማውን የተከታተሉትም ሰዎች ነግረውኛል። ጥፋቱ ግን የእኔ አይደለም፣ የደራሲውና የዳይሬክተሩ ነው። ደራሲውና ዳይሬክተሩ እንደ አቅሜ ቀለል ያለ ሚና እንድጫወት ቢሰጡኝ ኖሮ በደንብ ልጫወተው እችል ነበር፤ ስጠረጥር ግን ደራሲውም ዳይሬክተሩም አንድ ሰው ነው።

ድራማው ፍላጎት እንጅ ተሰጥዖ በሌለው ሰው መጻፉን ብዙ ሳይመራመሩ፣ ርእሱን ብቻ በማዬት፣ መናገር ይቻላል። "አኬልዳማ" ቃሉ መጽሀፍ ቅዱሳዊ ነው፤"የደም መሬት" ወይም "በደም የተገዛ ቦታ" ማለት ነው። ኢትዮጵያ ከግማሽ ያላነሰው ህዝቡዋ የእስልምና እምነት ተከታይ ነው። አኬል ዳማ የሚለውን ቃል ደግሞ በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ ተጽፎ እንደማይገኝ እርግጠኛ ነኝ። እንግዲህ ሙስሊም ወገኖች የቃሉን ፍች ለማወቅ አንድም ክርስቲያን ወገኖችን መጠዬቅ ሌላም መጽሀፍ ቅዱስን ማንበብ ሊኖርባቸው ነው። ከክርስቲያኑም ቢሆን የሚበዛው፣ ከተሳሳትኩ አርሙኝ፤

መጽሀፍ ቅዱስን፣ ሳጥኑ ውስጥ ቆልፎ የሚያስቀምጥ ነው። (ነፍሱዋን ይማርና እናቴ የጥንት መጽሀፍ ቅዱስ ነበራት፤ "እባክሽ አውጭውና ላንብብልሽ?" ስላት በጣም ትናደድ ነበር። በአንተ እጅ አይነካም፣ ሰይጣን ቤታችን ውስጥ እንዳይገባ መከላከያ ነው ትለኛለች፣ ምስኪን )።

አንድ ደራሲ ድርሰቱን ሲከትብ ተደራሲውን አስቀድሞ ማወቅ እንዳለበት የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መምህራችን ይነግሩን ነበር። የአኬልዳማ ደራሲ እንደሚመስለኝ የአማርኛ መምህር አልነበሩትም፤ ወይም አማርኛ ትምህርትን ይጠላ ነበር። ይህማ ባይሆን ኖሮ፣ ክርስቲያኑና ሙስሊሙ መጽሀፍ ቅዱስን እንዲቆፍር የሚያስገድድ አኬልዳማ የሚል ርእስ አያወጣም ነበር። ለነገሩ በህዝብ ቴሌቪዥን ለሚቀርብ ዝግጅት፣ የመንግስትን ሀይማኖታዊ አቋም የሚያንጸባርቅ ነገር መቅረብም አልነበረበትም።

የርእሱ ጅላንፎነት በዚህ ብቻ አያበቃም። የአኬልዳማ ስያሜ አመጣጥ እንዲህ ነው። የአስቆርቱ ይሁዳ እየሱስ ክርስቶስን በ30 ብር አሳልፎ ለገዳዮቹ ሸጠው፤ "ወላዋይ ፣ ከሐዲ እና ነዋዬ-አምልኮ ያለበት ሰው መጨረሻው አያምርም" እንዲሉ ፣ ይሁዳም ተጸጽቶ ገንዘቡን ለገዳዮቹ መለሰላቸው ። ሰዎቹ ግን ለይሁዳ አዝነው ይሁን የደም ገንዘብ ከእጃቸው እንዲወጣ በመፈለግ አላውቅም፣ ገንዘቡን ከይሁዳ ተቀብለው በስሙ የ30 ብር መሬት ገዙለት ። መሬቱም የደም መሬት ተባለ። ስንት ጋሻ መሬት እንደገዙለት ባለውቅም፣ ቦታውም ዛሬ በሂኖን ሸለቆ ደቡባዊ ክፍል ይገኛል።

እንግዲህ አኬልዳማ፣ አንድም ክህደትን ሌላም ደም ማፍሰስን ስንጨምርበት ደግሞ ገንዘብ መውደድን ይወክላል። ታዲያ በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ የክህደት፣ ደም የማፍሰስ እና የንዋየ- ፍቅር ምልክት ተደርጎ የሚታዬው ሰው ማን ነው? ብርሀኑ ነጋ ወይስ መለስ ዜናው? አንዳርጋቸው ጽጌ ወይስ በረከት ስምኦን?

"ዘመኑ ክፉ ነው" እንዲል የክርስቲያኖች መጽሀፍ፣ በአኬልዳማ ድራማ እዬሱስ ይሁዳ ይሁዳም እዬሱስ ሆነው እንመለከታለን። ተመስገን ደሳለኝ *አኬልዳማው የአይሁድ ወይስ የኢህአዴግ* በሚል ርእስ በጻፈው ጽሁፍ " በእርግጥ ያ በክርስቶስ ደም የተገኘው የ"አኬልዳማ ትርጓሜ እና የኢቴቪ የፊልም ጭብጥ ሀራምባና ቆቦ ነው… የፊልሙ ርእስ የፊልሙን ጭብጥ ሊወክል ይችል የነበረው በፊልሙ ላይ አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ብርሀኑ ነጋን አሳልፎ ሲሰጠው የሚታይ ቢሆን ኖሮ ነበር" ያለው ተስማምቶኛል።

ድራማውን ደጋግሜ ሳዬው ደራሲውን እርገመው እርገመው የሚል ሀጢያታዊ ስሜትም ይሞላኛል፤ በጨዋ ቋንቋ "ቀሽም" ድራማ ሰርቶ እኛን ተዋናዮችን "ለኦስካር" ሽልማት እንዳንታጭ ከልክሎናልና። አኬልዳማ ስለተዋናዮችና ስለ ጭብጡ ከሚናገረው ይልቅ ስለ ደራሲው ማንነት የሚናገረው ይበልጣል። የ Behavioral Science አጥኚዎች፣ "በአንድ ሰው አእምሮ ውስጥ ያለውን ነገር ማወቅ ባይቻልም፣ ነገር ግን ድርጊትን አይቶ ስለሰውየው የውስጥ ማንነት መናገር ይቻላል" ይላሉ። አኬልዳማም

በመለስ አእምሮ ውስጥ የታጨቀውን ነገር ሁሉ ፍንትው አድርገን እንድናይ አስችሎናል። እንደሚከተለው።

በድራማው የመለስ ዜናዊን የተጠራጣሪነት ባህሪ እናያለን። በ1996 ዓም መለስ ዜናዊ በተሳተፈበት አንድ ስብሰባ ላይ ለዘገባ ተገኝቼ ነበር። መለስን ለመጀመሪያ ጊዜ በአካል ያዩት ያኔ ነው። ፎቶ ግራፍ ለማንሳት ከመቀመጫዬ ብድግ ስል፣ አይኖቹ ተወርውረው አይኖቼ ውስጥ ገቡ። ካሜራዬን አስተካከልኩና ፣አደን ላይ እንዳለ ድመት፣ እየተራመድኩ ቀረብኩት። አይኖቹ ግን አሁንም እያንዳንዱዋን እንቅስቃሴዬን ይፈትሻሉ። ግራ ገባኝ፣ አቅጣጫዬን ቀየርኩ፤ አሁንም አለቀቀኝም። "የት ነው የማውቀው ብሎ ግራ ገብቶት እያዬኝ ይሆን ወይስ ፎቶ እንዳታነሳኝ እያለኝ ይሆን?" እንደምንም ታግዬ አንዴ ብልጭ አደረኩ። ጠባቂው ከመቅጽበት መጣና " ዞር በል በቃህ" አለኝ። ከጎኔ የተቀመጠው ጓደኛዬ በለሆሳስ " ሰውዬው እንዴት ነው የሚያይህ ጃል... አለቀልህ" አለኝ። ሳያልቅልኝ ወራቶች አለፉ።

እንደገና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የመሰብሰቢያ አዳራሽ ( ኢ.ሲ.ኤ) መውጫ በር ላይ የአፍሪካ መሪዎችን ሲሸኝ እና ለአንዳንድ ወጣቶች ፊርማውን ሲያኖር ደረስኩ። አንዲት ወጣት ፣ የቦሌ ልጅ መሰለችኝ፣ የመለስን ፊርማ እያዬች፣ እንደ እንቦሳ ትዘላለች ። ግራ ተጋብቼ እሷን ስመለከት "ፊርማ የማስፈረሙ ተራ" የኔ ሆነ ። ምን ላድርግ፣ ካሜራው እጄ ላይ፣ ማስታወሻ ደብተሬ ደግሞ

ቦርሳዬ ውስጥ ነው ። እንዳልፎገር አልኩና በፍጥነት ቦርሳዬን ከፋፍቼ ደብተሬን ሰጠሁት። ፈረመልኝ። ጠባቂው አሁንም ከመቅጽበት " በል ሂድ" አለኝ። "እባክህ ፎቶ ላንሳው ፍቀድልኝ?'" አልኩት። "አይቻልም፣ ዘወር በል" አለኝ ። ለመለስ ለማሳበቅ ዘውር ስል፣ ከጠባቂው የበለጡ አይኖች ገረፉኝ። መለስ በእርግጥም ከአጠገቡ መሆኔ አላስደሰተውም ነበር። ለካ ገና ድሮ "አሸባሪ" መሆኔን አውቆ ነበር። ዛሬ "ፊርማህን ደብተሬ ላይ ፈርመህልኝ ነበር እኮ" ብዬ ብለው ምን የሰማው ይሆን? ከሞት ተርፍኩ ብሎ ያስብ ይሆን?

አከታትልኩና በአዲስ ዜና ጋዜጣ ላይ "የመለስ ዳንሰኛ አይኖች" የሚል ይዘት ያለው ጽሁፍ ጻፍኩ፤ በእርግጥም መለስ ሲበዛ ተጠራጣሪ ሰው መሆኑን ዳንሰኛ አይኖቹን ብቻ በማዬት መናገር ይቻላል። የአኬልዳማው ጋዜጠኛ "ህይወታችን ሁሉ በስጋት እንዲሞላ አድርገውታል" ብሎ ያለው ይህንን ነው ያረጋገጠልኝ።

መለስ ተጠራጣሪ ብቻ ሳይሆን ፊቱ የማይፈታ፣ የውስጥ ሀዘን ያለበት ሰው ነው። በአካል ያዬሁዋቸው በርካታ የአገር መሪዎች ለምሳሌ ከአፍሪካዎቹ ፎልፎሌው አባሳንጆ፣ ሙሸራው ጋዳፊ፣ ካው ቦዩ ሙሴቬኒ ፊታቸው ላይ ይታይ የነበረው ፈገግታና ጨዋታ አይረሳኝም ። እንደ መለስ ፊታቸው የማይፈታ መሪዎች ቢኖሩ ጅንኑ ሙጋቤ እና ምናልባትም የሴኔጋሉ ዋዴ ናቸው። ሙጋቤ ሲራመድ እየተጀነነ ነው። አንድ ጊዜ ከጠባቂያቸው ርቀው የስእል

ኤግዚቢሺን ሲጎበኙ አገኘሁዋቸውና "ሚስተር ፕሬዚዳንት እባክዎ ጥቂት ጥያቄዎችን ልጠይቅዎ?" አልኩዋቸው ። በአይናቸው ጠርዝ አዩኝና ጉብኝታቸውን ቀጠሉ። በአኬል ዳማ ውስጥ የምንሰማው የጭንቀት ለቅሶ መለስ ዜናዊ ውስጥ የታጨቀውን ሀዘን ነው።

"ደራሲና ዳይሬክተር" መለስ ውሸታምም ነው፤ ውሸቱም ወደ ውሸት በሽታ (pathological liar) ተለውጦበታል። ይህ በሽታ በልጅነት እየዋሹ ከማደግ እንደሚመጣ የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። መለስ ከልጅነቱ ጀምሮ እስከ ሽምግልናው ድረስ ይዋሻል። በዚህም የተነሳ እውነትና ውሸትን ለይቶ ለማወቅ የሚያስችለው የአእምሮው ክፍል ክፉኛ ተበሳስቷል፣ ብዬ ብናገር ዋሾ አልባልም።

አኬላዳማ የመለስ የውሸት ባህሪ ነጸብራቅ ነው። በድራማው እንደቀረበው ሳይሆን ፣ እኔ ከፖለቲከኛ አንዱአለም አራጌም ሆነ ከምወደው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ጋር አንድም ቀን ፣ መንግስትን ስለመቀዬር አንስቼ ተነጋግሬ አላውቅም። ለስራ ጉዳይ ልደውልላቸው ስፈልግ እንኳን ፣ ስሜ መራራ ነው እያልኩኝ፣ ሌሎች የኢሳት ባልደረቦቼ እንዲደውሉላቸው ነው ሳደርግ የነበረው። አንድ ጊዜ ከእስክንድርና ከአንዱአለም አራጌ ጋር አጭር ቃለምልልስ ማድረጌን ብቻ አስታውሳለሁ። ከእነርሱ ይልቅ ከዶ/ር ነጋሶ፣ ከሌሎች የተቃዋሚ መሪዎችና ከኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣኖችና ጋር የተነጋገርኩት በእጅጉ ይበልጣል። ለአቶ በረከት ስምኦንና ለሽመልስ ከማል የደወልኩት ስልክ ለእነ

እስክንድርና አንዱአለም አራጌ ከደወልኩት ስልክ በብዙ እጥፍ ይበልጣል። የበረከት ወይም የሽመልስ  የሞባይል ስልኮች ቢፈተሹ እውነታው ገሀድ በወጣ ነበር።

መቼውንም የማልሸሽገው እውነት አለ፤ ብዙ ጊዜ፣ በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ላይ ከከፍተኛ የኢህአዴግ ባለስልጣናት ጋር ተነጋግሬዓለሁ፤ ኢሳትን እዬተመለከቱ አድናቆታቸውን የገለጡ፣ "ምን እንርዳችሁ፣ ከጎናችሁ ነን፣ እከሌን አገናኘኝ እባክህ" የሚሉ ከመምሪያ ሀላፊዎች እስከ ሚኒስትሮች አጋጥመውኛል፤ አንዳንዶችን ከሚፈልጉዋቸው ሰዎች ጋር አገናኝቻቸዋለሁ፤ ሌሎች ደግሞ አሁንም ድረስ ከእኔ ጋር እንደ ሁኔታው አመቺነት ይገናኛሉ። ከእነ እስክንድር ነጋና አንዱአለም አራጌ ጋር ባለኝ ግንኙነት "አሸባሪ" ከምባል ይልቅ ከኢህአዴግ ባለስልጣናት ጋር በመገናኘቴ "አሸባሪ" ብባል ኖሮ ተገቢ ክስ ይሆን ነበር። ኢህአዴግም ይህን ጠንቅቆ እንደሚያውቅ አውቃለሁ። ኢሳትን ከፖለቲካ ድርጅት ጋር የሚያይዘው ፣ እኔንም የማይገባኝን ሀላፊነት ሰጥቶ "ዝናዬን ከፍ" ያደረገው ፣ ለዚህ ይመስለኛል። ስራዬ መረጃ ቆፍሮ ማግኘት በመሆኑ፣ ተቃዋሚዎች " ሰላይ ይበሉኝም አይበሉኝም ኢህአዴግም "አሸባሪ" ይበለኝም አይበለኝም፣ ከኢህአዴግ ባለስልጣናትና ከተቃዋሚ መሪዎች ጋር መገናኘቴን እና እንዴት ነው አዬሩ ማለቴን አላቆምም።

ደራሲ መለስ ፈሪም ነው። የፍርሀት ምንጩ ደግሞ አምባገነንነቱ ነው።  አንድ አምባገነን መሪ የፍርሀት ካባ በላዩ

ላይ ከደረበ፣ እርሱ የሚመራው ህዝብ አለቀለት። አምባገነኖች እራሳቸው እየራዱ ሌላውም እንደነርሱ እንዲርድ ይፈልጋሉ። አኬል ዳማ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው ። መለስ የውስጥ ፍርሀቱን ፣ "አሁንም እንቅልፍ አይተኙልንም፣ አሁንም የሞት ድግስ እየደገሱልን ነው፣ ባለስልጣናትን ለመግደል ያሴራሉ" እያለ በጋዜጠኛው አፍ ሲናገረው እንታዘባለን።

መለስ ዜናዊ ስም አጥፊም ነው። የመለስ ቁጥር አንድ ገዳይ የነበረው ብስራት አማረ ፣ የዛሬን አያድርገውና እንዲህ ሲል ጽፎ ነበር " *መለስ እንደ መሪ ከቆሻሻ የፖለቲካ አሻጥር በተወሰነ ደረጃ ራቅ ብሎ ያስቀዬመውን በትእግስት ቻል አድርጎ ጓደኞቹን በጎኑ ለማቆዬት ሆድ ዬለውም። እንደ ህጻን ልጅ በተቆጣ ቁጥር ከመንደር ወጥቶ ስም በማጥፋትና የበቀል እርምጃዎችን በማቀጣጠል የራሱን ህይወትም በገዛ ራሱ በፈጠራቸው የማያውቁት ጠላቶች በስጋት እንድትኖር ዳርጓታል።"*

መለስ ዜናዊ ስም በማጠልሸት ታክቲኩ ዶ/ር አረጋዊ በርሄንና አቶ ግደይ ዘራጺዮንን ከጎኑ አስወግዷል። ብስራት አማረ ይቀጥልልናል ፤ " *ውለታውን መመለስ የማይችለው መለስ ዜናዊ ግን ከ1978 ዓም ጀምሮ ሁለቱንም የጥንት አሳዳጊው ጓደኞችን የተደረገውንና ያልተደረገውን ወንጀል በመቀባት ስማቸውን በማጥፋትና ከመሰረቱት ድርጅት ነጥሎ እንዲወጡ እና በስደት እንዲኖሩ በማድረግ የለዬለት የግላቸው ጠላት ሆኖ ቁጭ አለ።"*

መለስ ዜናዊ በዚህ እኩይ ድርጊቱ ገፍቶበት ስልጣን ከያዘ በሁዋላ ደግሞ አቶ ስዬን፣ ታምራትንና ሌሎች ለስልጣኑ ስጋት የሆናሉ ብሎ የፈራቸውን ሁሉ ስማቸውን እያጠለሸ እንዲወገዱ አድርጓል። በመለስ ከተፈበረኩት ስም የማጠልሻ ቃሎች መካከል "ተቸካይ፣ ቦናፓርቲስት፣ ጥገኛ፣ ጋጠ ወጥ፣ አሸባሪ፣ ነውጠኛ፣ ፌውዳል፣ ደርግ ኢሰፓ፣ ነፍጠኛ፣ ትምህክተኛ፣ ኢንተርሀምዌ ወዘተ..."ይገኙበታል።

ይህ የመለስ ስም የማጠልሸት ታክቲክ ከጎኑ ባሉት ሰዎች ላይ ብቻ ሳይሆን ተቀናቃኜ ይሆናሉ ብሎ ባሰባቸውም ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ሆኗል። በምርጫ 97 ማግስት መለስ ዜናዊ ጠላቴ ብሎ የፈረጃቸውን ሚስ አና ማሪያ ጎሜዝን" ከብርሀኑ ነጋ ጋር አንሶላ ተጋፈዋል" በማለት የተከበረ ስማቸውን አጎደፈ። ትንሽ ቆይቶም ይህን ቀፋፊ "ተረቱን" በሄራልድ ጋዜጣ ላይ አወጣው። በወቅቱ ሚስ አና ጎሜዝን ምን ተሰማዎት? ብያቸው ነበር። " ምንም አልተሰማኝም፣ በምን አይነት መንግስት እንደምትገዙ ብቻ ነው የገረመኝ" ነበር ያሉኝ። አኬልዳማ የመለስ ዜናዊ የማጠልሸት ባህሪ ቁልጭ ብሎ የታዬበት ድራማ ነው።

መለስ አሳሪና ግዳይም ነው። በመለስ እጅ ያልታሰረ ታዋቂ ፖለቲከኛና ጋዜጠኛ እምብዛም አይገኝም። በመለስ የግድያ ትእዛዝ በበረሀ የረገፉትን የቀድሞ የህወሀት ታጋዮች ቤት ይቁጠራቸው። በአኬልዳማ ድራማ በጋምቤላ፣ ኦሮሚያ፣ ኦጋዴን፣ አማራ፣ አዲስ አበባ፣ ደቡብ፣ ቤንሻንጉል ወዘተ ራሄልና ልጆቹዋ ስለፍትህ ሲያለቅሱ፤ ሲማጸኑ እንሰማለን።

እነርእዮት፣ እስክንድር ፣ አንዱአለም፣ ክንፈሚካኤል ፣ ውብሸት፣ ምትኩ፣ ወዘተ ፍትህ አጥተው ጸጉራቸውን ሲነጩ፣ እነ ደበበ ሸቱ፣ ከነፍሳችሁ ጋር ተጣሉ ሲባሉ እንመለከታለን። በሌላ በኩል ደግሞ ወንድሙ አቤልን ገድሎ መሄጃ አጥቶ እንደሚቅነዘነዘው ምስኪኑ ቃዬል አዳም መለስ ዜናዊም ከራሱ ጋር ተሳክሮ ከጠላቶቹና ከወዳጆቹ ጋር ሲላተም ፣ ሲቅነዘነዝ፣ ሲጨነቅ ሲጠበብ፣ እናያለን።- በደም መሬት ( አኬልዳማ)።

በአኬላ ዳማ መለስ ዜናዊ የሽፍትነት ባህሪው እና መንግስት የመሆን ባህሪው ሲላተሙበት እንታዘባለን። ጥሩ ሰው መስሎ ለመታዬት የሚያደርገው ባህሪው፣ በውስጥ ክፋቱ እየተሸፈነበት ሲጨነቅ፣ ሲናደድ፤ አንዴ ማኪያቬሌ፣ ሌላ ጊዜ ዊድሮው ዊልሰን ፣ አንዴ ጋዳፊ፣ ሌላ ጊዜ ማንዴላ፣ ሲሆን እናያለን ። ሳተናው ተማኝ በዬነ ይህን እውነታ በደንብ ታዝቦ በኢሳት ላይ እንዲህ ሲል ተናገረ "ከ20 ዓመታት በሁዋላ ፣ አራት ኪሎ ገብተውም፣ ከሰው ተቀላቅለውም፣ ከፈረንጅ ጋር ተገናኝተውም፣ ዛሬም አልተማሩም፣ ዛሬም እንደጫካው ጊዜ ያስባሉ።"

አኬልዳማ የእነዚህ ሁሉ የመለስ ዜናዊ ባህሪዎች የወለዱት ድራማ ነው።

ፋሲል የኔዓለም